በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁጥር 214291
ግንቦት 26 ቀን 2014ዓ/ም

ዳኞች፡-እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- ዳቫል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሐይማኖት መራ የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 104335 በሆነው ሰኔ 17ቀን 2013ዓ/ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤቶች በሰጡት ውሣኔ የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም ሲል የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መሰረዙ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው ተብሎ እንዲታረምለት አመልካች በመጠየቁ ነው፡፡

ጉዳዩ የይዞታ ክርክርን የሚመለከት ሆኖ ክርክሩ በተጀመረበት አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ይልማና ዴንሣ ወረዳ ፍርድ ቤት አመልካች ከሣሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሣሽ ነበሩ፡፡ አመልካች የካቲት 24ቀን 2012ዓ/ም በተፃፈ ክሱ በእጁ አድርጎ በሚጠቀምበት ስምንት ቃዳ ይዞታው ውስጥ ተጠሪዋ ከ2003ዓ/ም ጀምሮ የግንባታ ፈቃድና የይዞታ ማረጋጫ ሣይኖራት በ75 ካሬ ሜትር ላይ በ12ዚንጎ ቆርቆሮ የተሰራ ቤት ስርታ የአልኮል መጠጦችን፣ ምግቦችንና ልዩ ልዩ ሸቀጣቀጦችን እየሸጠች የመማር ማስተማሩን ስራው ላይ ችግር እየፈጠረችበት ለትምህርት ቤቱ ገቢ የሚያስኝ ይዞታውንም የያዘችበት መሆኑን በመዘርዘር ይዞታው በአንድ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

*አመት የሚያስገኘውን የሳር ግምት በአመት መቶ ብር ሆኖ የዘጠኝ ዓመት በድምሩ 900 ብር ከፍላ ቤቱን አፍርሣ እንድትለቅ እንዲወሰንባት ጠይቋል፡፡*

*ተጠሪ በበኩሏ በግምቱ የማትስማማ መሆኑን ገልፃ ሌላ ለእርሻም ሆነ መጠለያ ለመስራት የምትጠቀምበት ይዞታ የሌላት መሆኑ ተረጋግጦ ከአመልካች ይዞታ ውጪ ከሆነ መሬት ላይ በ1989ዓ/ም ተሰጥቷት ለ24ዓመታት በይዞታዋ አድርጋ የምትጠቀምበት መሆኑን፣ የሰብል ግምት የዘጠኝ ዓመት መጠየቁ ተገቢ አለመሆኑን በመዘርዘር ክሱ ውድቅ እንዲደረግላት ተከራክራለች፡፡*

*የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን መሬት ልትለቅ ይባል ወይስ አይገባም የሣር ግምትስ ልትከፍል ይገባታልን የሚለውን ጭብጥ ይዞ የግራ ቀኙን ማስረጃ መርምሯል፤ የወረዳው መሬት አስተዳደርም ማስረጃ እንዲሰጠው ትዕዛዝ ሰጥቶ በቀረበለት ማስረጃ ተጠሪ ከ1991ዓ/ም እስከ 2003ዓ/ም ድረስ በይዞታው ላይ ሽራ ዝርግታ ሻይና ዳቦ ስትሸጥ መቆየቷን በ2003ዓ/ም በ12ዚንጎ ቆርቆሮ ቤት መስርቷን፣ ለወጣቶች መሬት ሲሰጥ በአመራሩ ፈቃድ የተሰጣት ስለመሆኑ በምስክሮች ተረጋግጧል ካለ በኋላ ተጠሪዋ ከ1991ዓ/ም ጀምሮ ይዛ የምትጠቀምበትን መሬት ትክ ሣይሰጣት ልትለቅ አይገባም ሲል የአመልካችን ክስ ውድቅ አድርጓል፡፡ በዚህ ውሣኔ ቅር የተሰኘው አመልካች ይግባኝና የሰበር አቤቱታውን በየደረጃው ለሚገኙት የክልሉ ፍርድ ቤቶች አቀርቦ ስለፀናና ስለተሰረዘበት ይህን የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡*

*አመልካች መስከረም 10ቀን 2014ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታው ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ንብረት መሬት በመሆኑ ተጠሪዋ ባለይዞታ መሆንዋን እንዲሁም ግብር የምትከፍል መሆኑን የሚያረጋግጥ ምንም ዓይነት ማስረጃ ሣጣቀርብ ከ1991ዓ/ም ጀምራ በህገወጥ መንገድ መያዟን ብቻ መሰረት በማድረግ ትክ ሣይሰጣት ልትለቅ አይገባም ሲል መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው ተብሎ እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡*

*የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የሰበር ተጠሪ ሕጋዊ ይዞታ ማረጋገጫ የሌላት መሆኑ በስር ፍርድ ቤት ከመረጋጡም አንፃር አከራካሪውን ይዞታና ቤት ያለትክ ልትለቅ አይገባም ተብሎ የመወሰኑ ሕጋዊነት ለመመርመር ሲባል ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡*

*ተጠሪ በበኩሏ መጋቢት 1ቀን 2014ዓ/ም በተፃፈ መልሷ በጥቅሉ አመልካች ሳቃወማት ከት/ቤቱ ይዞታ ውጪ ቤት መገንባቷን፣ የስር ፍርድ ቤትም መሬቱን ልትለቅ አይገባም ሲል ውሣኔ የሰጠው ከ1989ዓ/ም የተሰጣት መሆኑን በሕዝብ አጣርቶ በማስረጃ አረጋግጦ መሆኑን በመዘርዘር ስር ፍርድ ቤቲ ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም ስትል ተከራክራለች፡፡ የግራ ቀኙ ክርክር በዚሁ ተጠናቋል፡፡*

*ከፍ በአጭሩ የተመለከትነው የጉዳዩን አመጣጥና በዚህ ችሎት የቀረበውን የግራ ቀኙን ክርክር ነበር፡፡ የስር ፍርድ ቤቱ ተጠሪ ለያዘችው መሬት ትክ ሣይሰታት ልትለቅ አይገባም ሲል በሰጠው ውሳኔ የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን በጭብጥነት ተይዞ ተመርምሯል፡፡*

*እንደተመረመረው አመልካች ክስ ያቀረበው የይዞታው አካል የሆነውን መሬት ስምንት ቃዳ ከሆነው የአመልካች ይዞታ ውስጥ ተጠሪዋ የግንባታ ፈቃድና የይዞታ ማረጋገጫ ሣኖራት በሕገወጥ መንገድ 75 ካሬ*

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ሜትር ላይ ቤት በመስራት የተለያዩ ሸቀጣ ሸቀጦችንና አልኮሆል መጠጥ በመሸጥ በትምህርት ስራው ላይ ችግር መፍጠሯን በመዘርዘር የገነባችውን ቤት አፍርሣ ይዞታውን እንድትለቅለት የተቋረጠ ጥቅም የዘጠኝ ዓመት እንድትከፍለው ጠይቋል፡፡

ተጠሪ በበኩሏ ለመጠለያም ሆነ ለሌላ አገልግሎት የምትጠቀምበት ሌላ መሬት ስላልነበራት መጠለያ እንድትሰራ

በት ከት/ቤቱ ይዞታ ውጪ ከወል መሬት ላይ በ1989ዓ/ም በቀበሌ አስተዳደሩ ተሰጥቷት በዚሁ መሬት ላይ ቤት ሰርታ ላለፉት 24 ዓመታት ሻይና ዳቦ በመሸጥ የምትተዳደር መሆኑን ዘርዝራ የአመልካችን ይዞታ በሕገወጥ መንገድ አለመያዟንገልፃ ተከራካራለች፡፡

የስር ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ማስረጃ አዳምጦ እንዲሁም የወረዳው መሬት አስተዳደር አጣርቶ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ በአመልካች በኩል የቀረቡት ምስክሮች ለክሱ መነሻ በሆነው ቦታ ላይ ተጠሪዋ ከ1991ዓ/ም ጀምሮ ይዛ መቆየቷን አሁን ላይ ት/ቤቱ ሲታጠር ወደ ት/ቤቱ ግቢ መግባቱን አረጋግጠዋል፡፡ አመልካች ባቀረበው ክስ ተጠሪዋ ከ2003ዓ/ም ጀምሮ ይዞታውን እንደያዘችበት የገለፀ ቢሆንም የራሱ ምስክሮች ከ1991ዓ/ም ጀምሮ ለክርክሩ መንስዔ የሆነው ይዞታ በተጠሪ እጅ መሆኑንና ይህ ይዞታ ወደ ት/ቤቱ የገባው ተጠሪ ከመያዟ በፊት ሳይሆን የት/ቤቱ ይዞታ ሲታጠር መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡  በአንፃሩ ተጠሪ ባቀረበቻቸው ምስክሮች በ1991ዓ/ም በቀበሌው የሚገኙ ወጣቶች መሬት ሲደለደሉ ተጠሪም ሻይ ሸጣ እንድትደደርበት አሁን የያዘችውን መሬት የተሰጣት መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡ መሬት አስተዳደሩ በበኩሉ ተጠሪዋ አሁን በያዘችው ይዞታ ላይ ከ1991ዓ/ም ጀምሮ ላለፉት 23 ዓመታት በመጀመሪያ ሽራ ዘርግታ ከ2003ዓ/ም ጀምሮ ደግሞ አሁን ያለውን ቤት በቆርቆሮ ስርታ ሻይና ዳቦ በመሸጥ ላይ መሆኗን ማረጋገጡን የሚገልፅ ማስረጃ ሰጥቷል፡፡

እንደሚታወቀው ሕግ ከሚፈቅደው ውጪ መብቱ የተጣሰበት ወይም ጥቅሙ የተነካበት ወይም የተወሰደበት ሰው ሕገወጥ ድርጊቱ ተወግዶ የተወሰደበት ንብረት እንዲመለስለት የደረሰበት ጉዳትም እንዲካካስለት ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ዳኝነት ጠይቆ ፍትህ የማግኘት መብቱ በሀገሪቱ ኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 37 እውቅና የተሰጠው መብት ነው፡፡ ይሁን እንጅ መብቱ በመጣሡ ወይም ጥቅሙ በመነካቱ የፍ/ብሔር ክርክር ያቀረበ ወይም መብት ወይም ግዴታ አለ ብሎ የሚከራከር ወገን መብቱ ወይም ግዴታው ስለመኖሩ የማስረዳት ሸክም ይኖርበታል፡፡ በማስረጃ ረገድም ግዴታው ወይም መብቱ መኖሩን ለማስረዳት ህጉ የተለየ ማስረጃ እንዲቀርብ ካላዘዘ በስተቀር ግዴታው መኖሩን በጽሁፍ፣ በምስክር፣ በህሊና ግምት በተከራካሪው ወገን እምነት ወይም በመሃላ ማስረዳት የሚቻል ስለመሆኑ የፍትሐ ብሄር ሕግ ቁጥር 2002 ይደነግጋል፡፡

በዚህም መሰረት የተካደ ፍሬ ነገርን በማስረጃ የማጣራት የዳኝነት ስልጣን በተሰጠው የስር ፍርድ ቤት ያቀረበውን ክስ በቅድሚያ የማስረዳት ሸክም ያለበት አመልካች ለክርክሩ መንስዔ የሆነውን ይዞታ ተጠሪዋ ከመያዟ በፊት ይዞታው የእርሱ ስለመሆኑ ማረጋገጥ ሲኖርበት ይህን ግዴታውን በአግባቡ ስለመጣቱ የጉዳዩ አመጣጥ አያስገነዝብም፡፡ በሌላ በኩል አመልካች የመንግስት ተቋም በመሆኑ በክልሉ የገጠር መሬት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 2(23) መሰረት የአመልካች ይዞታ የመንግስት ይዞታ በመሆኑ ይዞታውን መጠንና ጠረዋም በእርሱ ይዞታ ላይ ቤት የሰራች ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ስለማቅረቡ የውሣኔው ቅጅ አያስገነዝብም፡፡

በመሆኑም ማስረጃን የመመዘን የዳኝነት ስልጣን የተሰጠው የስር ፍርድ ቤት የአመልካች ክስ የተጠሪን የግል

ይዞታ ለመውሰድ በማሰብ የቀረ እንጅ ይዞታው ስለተወሰደበት የቀረበ ስለመሆኑ በማስረጃ አልተረጋገጠም በሚል ትክ ተሰጥቷት ካሣ ሣይከፈላት ይዞታዋን ለአመልካች የምትለቅበት መንገድ የለም ሲል የሰጠው ውሣኔና በየደረጃው የሚገኙት የክልሉ ፍርድ ቤቶች ማጽናታቸው ተገቢ ነው ከሚባል በስተቀር የሚነቀፍበት ምክንያት ስላልተገኘ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ውሣኔ

1) የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 104335 ሰኔ 17ቀን 2013ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ፤ የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 0325368 የካቲት 26ቀን 2013ዓ/ም የሰጠው ውሣኔ፣ የይልማና ዴንሳ ወረዳ ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥሩ ባልተጠቀሰ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረውን ክርክር መርምሮ ታሕሳስ 23ቀን 2013 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2) ይህ የሰበር ክርክር ያስከተውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ እልባት ስላገኘ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

አ/መ — የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም